በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥቅምት 15 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የምናየው ሂደት አሉታዊ ጠቀሜታ

ጥቅምት 15 2011

አሉታዊ ጠቀሜታ መባሉ ራሱ አነጋጋሪ ሊሆን የሚችል ነው ። ግን ክስተቶች ሁሌም ነጭና ጥቁር ብቻ አይደሉም ። ከመከራም ትምህርት ይገኛል ። አልነጋ ያለች ሌሊት ብዙ ታስተምራለች ። ወያኔ በሕዝብና በሀገር ላይ የመጣ መርገም ነው --ምንም ደግ ነገር አይወጣለትም ። ወያኔ ኢሕ አዴግን ለማስቀጠል መነሳት ጸረ ሕዝብ ሻጥር ለመሆኑ ክርክር የሚያስገባ ባይሆንም በተያዝው ሂደት ብዙ ተምረናል ።

አንደኛ ወያኔ ሊታደስ የሚችል አገዛዝ/ስር ዓት አለመሆኑን

2ኛ) የአድርባዩና ጸረ ሕዝቡ መንጋ ማነነት

3ኛ) የዘረኞቹ ይዘትና ድርጊት ምን እንደሆነም

4ኛ) ባእዳን በሀገራችን ላይ ያሴሩት ምን እንደሆነና ጉዳቱንም ለማወቅ ችለናል። ሆኖም አሁንም ሊደናገሩ የተዘጋጁና የሚታለሉ አለመጥፋታቸውንም በማየታችን ተምረናል ማለት ይቻላል ።ማን የት ቆሟል የሚለውም ጥርት ብሎ እየታየ ነው።

መለያው አጥር አገዛዙን በተመለከተ ያለው አቅዋም ነው ። ወያኔ ኢሓዴግን እናስቀጥላለን ወይም ይቀጥል የሚሉት ክፍሎች ወደዱም ጠሉም ሰልፋቸው ከሕዝብ ጋር ሳይሆን ከዘረኛውና ጨቋኙ ስርዓት ጋር ነው ። የሽግግርን ፍቱን መፍትሔነት በሰበብ አስባቡ ተቃርነው በወያኔ ስር ምርጫ በሚል ሹሞቹን ለማስቀጠል የታሰበው የሕዝብን ፍላጎት ይጻረራል። ሽግግር የሚባለው እኮ ልዩነት በመኖሩ ይህንን በውይይታ ድርድር በጋራ ውሳኔ ለመቅረፍ ለመጣር ነው ።ሽግግር ግጭትን ለማስወገድና ለውጥን ለማረጋገጥ ወሳኝ መንገድ ነው ።ገንጣይና የአንድነት ጠበቃ በድፍንፍን ሊደባለቁ አይችሉም ። በሜንጫ አማራ ክርስቲያኑን ካልፈጀን ባዮች እብዶችና ከተጠቂው ሕዝብ ሊሰምሩም መጠበቅ እለበትም ።የተያዘው ወያኔያዊ አማራጭ ለወያኔ ማገገም እንደረዳ እያየነው ነው ። ሽግግር ለስልጣን አቋራጭ ፍለጋ ነው ይሉናል። ይህ በተገላቢጦሽ ነው ። ያለውን ስርዓት ማስቀጠል ነው የለውጥን ትግል አደናቅፎ የሚያስቀር፤የተጠላውን የሚያስቀጥልና ስልጥንን በሹሞቹ እጅ የሚያከርም ። ምርጫ ከተባለ ከሁሉም ቀደም የወያኔ ህገ መንግስት ተብዬ ሰነድ መቀየር አለበት። ከሽግግር ሂደት በኋላ ነው ምርጭ የሚባለው በተሻሻለ ህግና ስነ ስርዓት መሰረት መደረግ ያለበት ። ደም የፈሰሰው የመለስን መንጋ በወጣት ጀሌዎቹ ለመተካት አለመሆኑን እንኳን ሕዝብ ሹሞቹ ራሳቸውም ጠንቅቀው የሚያውቁት ሀቅ ነው ማለትም እንችላለን ። አዲሱን ሹም ራሱን ብንወስድ ለተወሰነ ጊዜ ብዙዎችን ሊያታልል ችሎ ነበር ። በሬ ሆይ በሬ ሆይ ያልናቸው ጸጉራቸውን ንጭተውብን ተናደውብንላ ። ፈጣሪያችን የሰጠን መሪ ነው ብለውም አላግባብ የተናገሩ ነበሩ ።ብዙ ጊዜ ሳይፈጅ ቢከቱት ተልባ--ያው ወያኔ--መሆኑም ሊያዩ ችለዋል ።በሹሞቹና በወያኔ መሪዎች አለ ተብሎ የተራገበውም ቅራኔ መሰረታዊ አለመሆኑን ለመረዳት ረጅም ጊዜ አልጠየቀም ።በርግጥ ዛሬም የማደናገሩና የምሻሻፉ ዘመቻ በባዕዳን ተደግፎ ቀጥሎ ይገኛል።ነገር ግን ዜጋዎች ይበልጥ እየነቁባቸውና እያወቁባቸው መጥተዋል ማለት እንችላላን ።ትምህርት ተወስዷል፤ ትምህርት ተገኝቷል ።

ከአዲሶቹ ሹሞች ምን አገኘን ? ረብሻና ብጥብጥ፤ግድያና ፍጅት፤የተጠናከረ ጸረ አማራነት፤ብራዩ፤አላማጣ ፤ጊዴዎ ቤኑ ሻንጉል። ለሕዝብ ይህ ነው የሚባል ጠቀሜታ ያልሰጡና ገለባ ዘረኛም የሆኑ ቡድኖችን ጋብዘው ሀገርን ከማክሰራቸው ባሻገር ለሜንጫው መንጋ አመቺ ሁኔታ ፈጥረው ለጭቁኖች መገደል ምክንያት ሆነዋል ። ጥቂቶች ለጠበል ያህል ተፈትተው ብዙሃኑ አሁንም በስየል እየማቀቁ ናቸው ። ምን አተረፍን? የተዘባረቀ ልፈፋ ። ወደ ሽግግር እርምጃ ሊወሰድ ቀርቶ ባለህበት ርገጡ ሰፍኖ ሀገር ወዳድ ወጣቶች ሳይቀሩ ሲሰየፉ፤ሲገደሉና ሲጋዙ ለማየት በቅተናል ።ለእስር የተዳረጉ ወገኖቻችን በጥቂቶች መፈታት ተሸፍኖ ስቃያቸው እንደቀጠለ ነው ። የወያኒን ዘረኝነትና በላይነት ሌሎች በግሃድ ሊተኩ ሲራወጡ እያየን ነው ። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መሆኗ እየተካደ ነው ። ራያ ትግሬ ነህ ተብሎ እየተገደለ ነው ። ሀገራችን ለአረቦችና ለሻዕቢያ ብዝበዛ ተጋልጣለች ። ሹሞቹ ተገልብጠው ከወያኔ ገጥመዋል ።ለስልጣናቸው ማጠየቂያቸው ሕዝብ ሳይሆን ወያኔና ስርዓቱ ናቸው ። ዘረኝነት በቆጥ ሰፍኖ ታድሶ፤ከፍቶና አውሬነትንም ተላብሶ ሰፍኖብናል ።ሀገራችን ለአደጋ ተጋልጣለች ብንል ማጋነን አይሆንም ።ጥምብ አንሳዎችም ከየቦታው ተጠራርተው በመከራ የደከመ ሕዝባችን ላይ ጥርሳቸውን አግጠው ተሰማርተዋል ። ቅርጫ! በዚህ ዘግናኝ አሳዛኝ ኮረብታ ላይ ነገስኩ ብሎ ያለው ያው ወያኔ ኢሕ አዴግ ነው ። አደናጋሪ ቃላት ካባቸው ሲገፈፍ ያው ቃናቸው የወያኔ መሆኑን ማወቅ እንችላለን ። ደም የገበርነው ገዳዮቻችን በአዲስ መልክ እንዲቀጥሉብን አልነበረምና የአደናቃፊው ሹም ሚና ለኢትዮጵያ ጠንቅ ነው ።በአጭሩ መቀጨቱ የሀገር አድን ትግላችን አካል መሆን አለበት ።

አሁንም ግን ከወያኔ ግፈኛ አገዛዝ ተላቆ ወደ ዴሞክራሲያዊና ሁሉን አሳታፊ ሂደት ለመሸጋገር ጊዜ አለ ። ይህ ግን ኣኔ ኢሕ አዴግን የማስቀተልን ዕቅድ እርግፍ አድርጎ መተውን የግድ ይላል ።ቅድመ ሁኔታ ነው ። አዲሱ ሹምና ጓደኞቹ ያላቸውን የስልጣን መቀጠል ውጥን መተው ይኖርባቸዋል ።በነጻና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ የመመረጣቸው ሁኔታ ካለ ለማየት ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸው ማለት ነው ። ሌሎችም እንዲሁ ።ስልጣን አለንና በጉልበት እንቀጥላለን ብሎ መመኘቱ መጨረሻው ያው መንኮታኮት ነው--ብዙ ጥፋት ካደረሱና ወንጀል ውስጥ ከተጨማለቁ በኋላ ።የኢትዮጵያ ህዝብ ነቅቷል፤ ሚጠቅመውን ሚጎዳውንም ለይቷል ።ከእንግዲህ ወዲህ ማንም ሊጋልበው የሚችል ወይም ጫንቃውን ለቀነበር የሚያመቻች አይደለም ። እርማቸውን ቢያወጡ ደግ ነው ሁሉም ዘረኞችና አምባገነኖች ። ወደ ገደሉ ከመገባቱ በፊት ዝብርቅርቁናና ማወናበዱን አክትመው ሁሉንም ሀይሎች የሚያሳትፍ የሽግግር ሂደት ቢጀመርና በዚህ መሰረት በጋራ ስምምነትና ቀጥሎም በሕዝብ ወሳኝነት መፍትሔ መፈለጉ የተሻለና ብቸኛ አማራጭ ሆኖ ይገኛል ። የግንጠላ አቀንቃኞችን በስፋት ማሰማራትና ያበዱ ዘረኞችን በሕዝብ ላይ ማስፈንጨት ሀገርን ከጥፋት አያድንም ።የርስ በርስ ግጭቱ ደግሞ በእኛ ፍላጎት ይካሄዳል ይከናወናል ብሎ ማሰቡም ጎጂ ስህተተት መሂኑን ከወዲሁ ማውቅ የሚገባ ነው ። ዝግ ሆኖ መቆየት ያለበትን የዲያብሎስ ሰንዱቅ የሞከፍቱ ምን እንደሚመጣባቸው ማወቅ አይችሉምና ከዚህ ድርጊት ቢቆጠቡ ይበጃቸዋል እንላለን ። አቅም የለሽ ነው የተባለውና የሚጠቃው ጭቁን በተነሳ ጊዜ መደበቂያ አያገኙም፤ ዛሬ በዘረኛ ዕብሪት የሚፈነጩት ።

መለእከታችን ድላችንን ተቀምተናልና ሀገራችንን ለማዳን ትግላችን ይቀጥል የሚል ነው።ትግላችን ከቆመ ይጨፍሩብናል፤ ወያኔ እንደገና ያንሰራራብንና አዲሱን ሹም እነ ደብረጽዮን መጋዣ አድርገው ሊጠቅሙበት ምቹ ዕድል ያገኛሉ ። የአዋሳው ጉባኤ ተብዬ ቧልት ይህን ግልጽ አድርጎታል ። አዲሱ ሹም የወያኔዎች ሹም ነው።ከጠባቦችና ባለሜንጫዎች ጋርም ያለው ቅርበት አጠያያቂ ነው ። መታለል የለብንም።የብሩራዩ ገዳዮችን ሳይዝ ይህን የተቃወሙትን ሀገር ወዳድ ወጣቶ አግዟል ።

ለማደናገር የተወሰኑትን ለቀቅኩ ብሎ በአውሮፓ ሀገር ወዳድች ሰልፍ እንዳያደርጉበት ቢጥርም ተንኮሉን በመረዳት በየሄድበት ሁሉ ተቃዋሞ መስፋትና በሀገራዊ መፈክሮች ዙሪያ ወንጀለኛ አገዛዝ ይወገድ መባል አለበት ። ዜጎች ፈጣሪያችን ያሉትን ካልጠሉ በስተቀር ፈታሪ እነዚህን ዓይነት አውሬዎች-ወያኔዎች ሰጠን ብለው ሊያምኑ አይፈቀድላቸውም ።ሐጢያት ነው ብንል ትክክል ነው ።ሐራም ከመጀመሪያው። ወያኔ ኢሕአዴግ የነካው ሁሉ የማይጠራ ሽንፈላ መሆኑን እነ ታምራት ላይኔ፣ ሌንጮ ለታ ወዘተ በበቂ አረጋግጠውልናል ። ቹሞቹ የሽግግር ሂደትን ተቀብለው የሕዝብ ስልጣን የሚረጋግጥበትን ምርቻ ቢቀበሉ ደግ ይሆናል ። ካልሆነ ግን ታሪክ በአጥፊነት ትመዘግባቸዋለች ። በዙሪያቸው የተኮለኮሉት ከንቱዎችም ከጥፋት የሚያድኗቸው አይሆኑም ።

የሽግግር ሂደት አማራጭ የለሽ ብቸኛ መፍትሔ ነው ።

ጻረ ወያኔ ጻረ ኢሕ አዴግ ትግላችን ይፋፋም !!

ድል ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት !!